# የነብይ ያለህ !

የገንቻው !

ነብዩ መሃመድ በመረቃት ምድር፤
ፍትህ ሰላም ፍቅር በሻተባት ደብር፡
እንዴት በደል ይንገስ ትውልድ የሚቀብር፤
አጥፍቶ እሚያጠፋ የእንግዴ ልጅ ጠፍር፤
ዘር ሽል እሚያመክን በላዕዪሰብ ፍጡር፤
እንዴት ወልዳ ትምከን ልጅ ገብራ አዳር፤
**ኧረ የአገር እናት አትነሳም ወይ ጡር።**

በሰው ዘር መገኛ ጥንታዊት ሃገር፤
ስለ ዓለም በዓለም ላይ ዘመን የሚዞር፤
ታሪኳን ታዕምሯን ክብሯን እንዳይነገር፤
ስሟን የሚያጠፋ እንዴት ጉድ ይኑር፤
በእምነት የቆረበች አዛውንት ምድር፤
የክርስትና እምነት የቀደምት መንደር፤
**በካህዲያን ተሳስራ እንዴት ኋላ ትቅር።**

እምነት የገመደች ግንጉን እትብት ክር፤
መንታ የጻነሰች ዞትር ነፍሰ ጡር፤
ወላዲት ኢትዮጵያ ሽለ ሙቅ ሃገር፤
የእስላም ክርስትና የሃይማኖት መዋቅር፤
ፈርጥ እንቁ ልጆቿ ተፈጥሮዋ እሚያምር፤
ታላቅ ገድል ታሪኳ ክብሯ እንዳልነበር፤
እንዴት ወሬ ታንገስ ገዳይ ቁምነገር፤
ሰላም አደፍርሶ አሳቦ ሽብር፤ እሚቀስፍ አድባር፤
የከዳ፤ የካደ ቃልኪዳን ሳያስር በግዝት ላያድር
በመለኮት ገዳም በሼሆቹ መስጊድ በመናኞች እጥር፤
በቤተክህነቱ ባህታዊ ካህን ሰላይ የሚቀጥር፤
በመጅሊስ፤ካርድሬዎች ሸፍጥ ኢማም ፤ሹምሽር፤
እውነት፤ እምነት፤ ጽናት በቁም የሚቀብር፤
ቅጥፈት ክህደት ፈጥሮ አዋጅ እሚነገር፤
ሞቱን ሲያረዳን ነው ወያኔ መንደር፤
**ቀርቧል ትንሳዔያችን የሰማው በምድር።**

ከዓመት በላይ መስጊድ በእምነት ቢማጸኑ፤
ለሃገር፤ ለሃይማኖት፤ ለሰላም ቢጸኑ፤
እስራት ግድያ አፈና ነው መጥኑ፤
ቀን በለስ የሰጠው ጨለማ ተገኑ፤
የቅጥፈት ድራማው የተንኮል ውጥኑ፤
ወያኔ ተጋልጧል ገሃድ ወጣ እርቃኑ፤
"ጃሃድ ሃረካዊት"፤ “አኬልዳማ” ተውኑ፤
የሕዝብ አንጡራ ኃብት ከንቱ እያባከኑ፤
በሃሰት ፈጠራ የመንግስት ተብዬ የጥፋት ብይኑ፤
ነገም ተነግወዲያ የሃቄት ተክህሎ "ተዋህዶ -ምኑ?"
ቆራርጠው ቀጥለው ውሸት ሊያላዝኑ፤
እንዲህ ናቸው ሽፍቶች " ጥበብ የተካኑ"፤
**ሁለት አስርተ ዓመት ድሎት የዘመኑ።**

የዋሻ ስልጡኖች "በቁጭ በል" ሊያቀኑ፤
የበቀል በቀቀን እያቀነቀኑ፡
አስረው፤ገርፈው ውሸት ተውኔት እያስጠኑ፤
ፊልም ይሰሩብናል እያጠነጠኑ፤
የአብራካችን ክፋይ ደም አጥንት ሲያመቅኑ፤
ደንዝዘን ፤ ቀዝዘን ንቀውን ሲዝናኑ፤
በደል ከፋታቸው ልክ አልፏል መጠኑ፤
ሃያ ዓመት ቋቅ አለን ውሸት ሲከሽኑ፤
**ኧረ ነብይ የት ነህ?፤ ተነስ ምዕመናኑ!፡፡**

- *ለሰላም፤ለአንድነት፤ለሃገር፤ለፍትህ፤ለሃማኖት ነፃነትና ለሕግ መንግሥቱ መከበር ሲሉ በሃቅና በጽናት ቆመው ከወንበዴው የወያኔ መንግሥት ተብዬው እጅግ ልቀውና በልጠው በዓርዓያነት ሲታገሉ፤ በዚህ ጨካኝ ቡድን ታፍነውና በግፋ ታስረው እየተሰቃዪ እጅ እግራቸውን ተቀፍደው በቅርቡ ደግሞ ‘የጃህዳዊ ሃረካት’ በሚል የሲራ ድራማ ለሚሰራባቸው እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆችና የእስልምና ጉዳዮች መፍትሄ አፈላላጊ ኮሞቴዎች መታሰቢይ ትሁንልኝ።*
- *የተከበርክ ኢትዮጵያዊ ሁሉ! ይኽ ግፋና በደል አይበቃህም ወይ? በእያንዳንዳችን ቤተሰብ አለዚያስ በእራሳችን እስኪደርስ ነው ወይ፤እያጎረመርምክ/ን የምትኖረው፡ ለምንስ ከሌላው የአረብ አገር ሕዝብ የነጻነት አርነት አትማርም/አንማርም ????*
- *ከዚህስ የከፋ ምን እስኪመጣ ነው የምት/ንጠብቀው???*

yegonchaw@yahoo.co.uk 06.02.13